የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ከጥር 7 - ጥር 13፤ 2017 ዓ.ም
JANUARY 15- 21, 2025 G.C


## 1.ከ78 ዓመታት በኋላ ነጋዴው መሪዎቹን መርጧል የተባለለት የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ጠቅላላ ጉባዔ

**ሪፖርተር፡ January 19, 2025**

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አወዛጋቢ ሒደቶች የነበሩትን ጠቅላላ ጉባዔ ባለፈው ሐሙስ ጥር 8 ቀን 2017 ዓ.ም. አካሂዷል፡፡

በዚህ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ከዚህ ቀደም አባል ያልነበሩና ጉባዔው ሊካሄድ አንድ ቀን ሲቀረው ፎርም ሞልተው አባል የሆኑ ከየክፍለ ከተማው የተወከሉ ነጋዴዎች የጠቅላላ ጉባዔው አባላት በመሆን፣ ንግድ ምክር ቤቱን ለቀጣይ ሁለት ዓመታት የሚመሩ ፕሬዚዳንትነት፣ በምክትል ፕሬዚዳንትነትና የቦርድ አባላት ተመርጠዋል፡፡ በዚህም ምርጫ የአዲስ አበባ ነጋዴዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት የሆኑት ወ/ሮ ዘሀራ መሐመድ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሆነው ተመርጠዋል፡፡ ወ/ሮ ዘሀራ 355 ድምፅ በማግኘት የተመረጡ መሆኑን ንግድ ምክር ቤቱ ገልጿል፡፡ ከወ/ሮ ዘሀራ ጋር ለፕሬዚዳንትነት ተወዳድረው የነበሩት በተሳናባቹ ቦርድ አባል የነበሩት ወ/ሮ ሳራ ሰለሞን ናቸው፡፡ እሳቸው 34 ድምፅ አግኝተው ቢሸነፉም በአዲሱ ቦርድ ውስጥ ተካትተው በቦርድ አባልነት እንዲያገለግሉ የተመረጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ በፕሬዚዳንትነት ለውድድር ከቀረቡ ሁለቱ ዕጩዎች ሌላ ለፕሬዚዳንትነት ለመወዳደር ዝግጅት እያደረጉ የነበሩትና በማኅበራዊ ሚዲያዎችም ራሳቸውን ሲያስተዋውቁ የነበሩት ዓለማየሁ ንጋቱ (ኢንጂነር) ምርጫው አንድ ቀን ሲቀረው ራሳቸውን ያገለሉና በዕለቱ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ሳይገኙ ቀርተዋል፡፡ በምክትል ፕሬዚዳንትነት የተመረጡት አቶ አበበ ጉርሜሳ መሆናቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያስረዳል፡፡

በንግድ ምክር ቤቱ ታሪክ ባልተለመደ ሁኔታ መካሄዱ የተለገጸው ይህ ጉባዔ፣ ለዓመታት የንግድ ምክር ቤቱ አባላት በዚህ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ እንዲሳተፉ አለመደረጉም ከመገለጹም በላይ ጠቅላላ ጉባዔው በፍርድ ቤት እንዲታገድ ደርሶ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ሆኖም ጠቅላላ ጉባዔው እንዲታገድ ለፍርድ ቤት ያመለከቱት የተሰናባቹ ቦርድ አባል ክሳቸውን በማንሳታቸው የታገደው ጉባዔ ሊካሄድ ችሏል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/137478/

## 2. በነዳጅ ማደያዎች የቴሌብር ወኪሎች እንዲነሱ ትዕዛዝ ተላለፈ

**ሪፖርተር፡ January 15, 2025**

ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በሁሉም የነዳጅ ማደያዎች ሲሠሩ የነበሩ የቴሌብርም ሆነ የማደያ ወኪሎች እንዲነሱ ሲል የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ለሁሉም የነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች፣ ለኢትዮ ቴሌኮምና ለኢትዮጵያ ነዳጅ አዳዮች ማኅበር በላከው ደብዳቤ አስታወቀ፡፡ ባለሥልጣኑ መንግሥት የነዳጅ ግብይትን በጥሬ ገንዘብ ወይም በካሽ የነበረውን ለማስቀረት ከመጋቢት ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ፣ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር ወደ ዲጂታል ግብይት ዘዴ የቀየረ መሆኑን ገልጾ፣ በዚሁ መሠረት ተጠቃሚው ማኅበረሰብ ሲስተሙን እስኪለምድ ድረስና የግብይት ሥራውን ለማቀላጠፍ ሲባል የቴሌብር ወኪሎች በማደያዎች እንዲመደቡ መደረጋቸውን አስታውሷል፡፡
ማኅበረሰቡ ስለሲስተሙ በበቂ ሁኔታ ግንዛቤ ያገኘ ስለሆነ ባለሥልጣኑ ነሐሴ 23 ቀን 2016 ዓ.ም. በደብደቤ ቁጥር 2.1/132/2016 በሁሉም ነዳጅ ማደያዎች የሚገኙ የቴሌ ተወካዮችም ሆነ ነዳጅ ማደያው በራሱ ያስቀመጣቸው የቴሌብር ወኪልነት እንዲቆም ያሳወቀ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያልቆመ መሆኑን ማረጋገጥ ችያለሁ ብሏል፡፡

ስለዚህም ከጥር 1 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ በሁሉም የነዳጅ ማደያዎች ላይ ምንም ዓይነት የቴሌ ብር ወኪል ሆነ የማደያ ወኪል እንዳይኖር ትዕዛዝ አስተላልፌያለሁ ብሏል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/137390/

## 3. በተለያየ ምክንያት ስራ አቁመው የነበሩ ከ625 በላይ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ስራ እንዲመለሱ ተደርጓል- ሚኒስትር መላኩ አለበል

**ኢኤአ ጥር 13/2017**

በተለያየ ምክንያት ስራ አቁመው የነበሩ ከ625 በላይ አምራች ኢንዱስትሪዎች በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ አማካኝነት ወደ ስራ መመለሳቸውን የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል ገለጹ።
የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የእቅድ አፈፃፀም የስትሪንግ ኮሚቴ ውይይት እየተካሄደ ነው።
የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል በዚሁ ወቅት እንደገለፁት የኢትዮጵያ ታምርት ሀገር አቀፍ ንቅናቄ ወደ ስራ ከገባ ጀምሮ በተለያየ ምክንያት ስራ አቁመው የነበሩ ከ625 በላይ ኢንዱስትሪዎች ወደ ስራ ተመልሰዋል።
የአምራች ኢንዲስትሪዎች የማምረት አጠቃቀም 46 በመቶ የነበረ መሆኑን የጠቀሱት አቶ መላኩ፥ ንቅናቄው ከተጀመረ አንስቶ በአማካይ የማምረት አቅም ወደ 61 በመቶ መድረሱን ገልጸዋል።
ንቅናቄው ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በመንግስት ትኩረት እንዲያገኝና በዘርፉ ችግሮች ዙሪያ ተከታታይነት ያለው ውይይት በማድረግ ለችግሮቹ የመፍትሔ ባለቤት በመሆን በጋራ መስራት በመቻሉ የማምረት አቅም አጠቃቀም፣ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች መተካት፣ በራስ ምርት የመኩራትና የመጠቀም ባህል እየተሻሻለ መምጣቱን ጠቅሰዋል።
https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5825260

## 4. ኢትዮጵያ ከጂቡቲ ጋር ያላት የጸና ትብብር ለጋራ ዕድገት ምቹ መደላድል የሚፈጥር ነው-ካሳሁን ጎፌ(ዶ/ር)

**ኢዜአ ጥር13/2017**

ኢትዮጵያ ከጂቡቲ ጋር ያላት የጸና ትብብርና የመሠረተ ልማት ትስስር ለጋራ ዕድገትና ለአዳዲስ ዕድሎች ምቹ መደላድል የሚፈጥር ነው ሲሉ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) ገለፁ፡፡ ሚኒስትሩ፥ ዛሬ በኢትዮ-ሎጅስቲክስ የዘርፍ ማኅበራት በተዘጋጀው የቢዝነስ ማኅልበቻ ኮንፈረንስ ላይ ተገኝተዋል።በዚህም ከጂቡቲ ጋር ያለውን የንግድ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነት አስፈላጊነት እና የኢትዮጵያ መንግስት በቀጣናው የንግድ እድሎችን ለማሳደግ ያለውን ቁርጠኝነት አረጋግጠናል ብለዋል።

ከጂቡቲ ጋር ያለን የጸና ትብብርና የመሠረተ ልማት ትስስር ለጋራ ዕድገትና ለአዳዲስ ዕድሎች ምቹ መደላድል የሚፈጥር መሆኑን በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ጠቁመዋል።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ ተግዳሮቶችን በማስወገድ ከአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ስምምነት ጋር የሚስማማና አስተማማኝ የትብብር ማዕቀፍን እውን ለማድረግ በትጋት እየሰራ ነው መሆኑንም ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የማኑፋክቸሪንግና ግብርናን መሰረት ያደረገና ብዝሃነት ያለውን የውጭ ንግድ ለማስፋት ለሚሰራው ስራ ጂቡቲ ስትራቴጂክ አጋር መሆኗን ነው የገለጹት።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5824703

**5. Ethiopia Earns 908 Million USD from Coffee Export in Six Months**

**ENA: January 20, 2025**

Ethiopia has secured 908 million USD from coffee export during the past six months, according to the Ethiopian Coffee and Tea Authority (ECTA). Briefing the media today, Deputy Director General of ECTA Shafi Umer stated that the country has exported more than 200,000 tons of coffee during the stated period as production and productivity has been massively increased in the sector. For the deputy director general, the country has been undertaking remarkable reform in the coffee sector in recent years particularly focusing on increasing quality, production and productivity. For the deputy director general, the country has been undertaking remarkable reform in the coffee sector in recent years particularly focusing on increasing quality, production and productivity. Following all the various reforms taken by the government and stakeholders pertinent to the sector, the country secured 908 million USD by exporting more than 200,000 tons of coffee during the past six months.

The plan set for the stated period was to attain 714 million USD by exporting over 133,000 tons of coffee, according to the deputy director general.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5821628

**6. Ethiopia's Debt to GDP Ratio Declines to 13.7 Percent**

**ENA: January 14/2025**

Planning and Development Minister Fitsum Assefa said Ethiopia's debt to GDP ratio has declined to 13.7 percent following the implementation of the comprehensive economic reform. In her briefing regarding the achievements of the macroeconomic reform and next endeavors, the minister noted that the government has been implementing new economic and social policy perspectives to address systematic and structural problems. The new policy perspective focuses on a multi-sectoral approach and prioritizes responding to fair share of citizens by implementing inclusive system, she added.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5792220

**7. Zahara Mohammed Elected as New President of Addis Ababa Chamber of Commerce**

**Capital: January 20, 2025**

In a significant development for the Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Associations (AACCSA), Zahara Mohammed has been elected as the new president following the conclusion of the Chamber's 18th regular general meeting. This marks a historic moment as Zahara becomes the second female president to lead the council since its establishment in 2018.

The election, held on January 17, 2025, saw Zahara Mohammed secure her position with an impressive 355 votes. She will serve a two-year term, succeeding Mesenbet Shenkute, who has held the presidency for six years. Mesenbet was first elected during the 14th General Assembly in October 2018 and was re-elected in subsequent years. However, at this latest assembly, she stepped down, paving the way for Zahara's leadership.

Alongside Zahara, Abebe Gurmesa was elected as Vice President, further solidifying the leadership team for the next term. The newly elected board members include Sarah Solomon, Addisu Getaneh, Damte Dagne, Zahara Ahmed, Mesfin Gared, Girumnesh Yimer, Habtamu Hailu, and Aycheluhem Kebede.

This election is particularly noteworthy as it represents a shift towards greater inclusivity within the AACCSA. For the first time, the entire community participated in electing its leadership. Previously, board members were selected by a smaller group of insiders, leading to calls for reform and transparency within the organization. The recent changes come after months of discussions and an audit aimed at addressing internal issues within the Chamber.

https://capitalethiopia.com/2025/01/20

**8. Ethiopia Showcases Investment Potential in High-level Meeting with Chinese Delegation**

**ENA: January 17, 2025**

Ethiopia's Minister of Planning and Development, Fitsum Assefa, welcomed a Chinese delegation led by Lu Hao, President of the Development Research Center of the State Council of the People's Republic of China, to discuss deepening China-Africa collaboration and shaping the vision for the soon-to-be-launched Global South Research Center.

Fitsum emphasized China's indispensable role as Ethiopia's largest source of foreign direct investment (FDI) and a key trading partner, particularly in imports.

She expressed Ethiopia's desire to expand its agricultural exports to China, pointing to untapped opportunities that could foster mutually beneficial trade ties.

Central to the discussions were Ethiopia's sweeping macroeconomic reforms. Fitsum detailed the government's bold initiatives, including the floating of the birr, opening the financial sector to foreign players.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5809820